# የተቀነሰው የሜትሮ ባቡር አገልግሎት ባለበት ሁኔታ ይቀጥላል

ቪዲዮ፡- <u>የሜትሮ ጋዜጣዊ መግለጫ - ጥቅምት 22፣ 2021</u>

ሜትሮ (Metro) ከደህንነት ባለስልጣናት ጋር በመተባበር 7000-ሲሪየስ የባቡር ተሽከርካሪዎችን ወደ መንገደኞች አገልግሎት ለመመለስ እና የባቡር አገልግሎቱን ሙሉ በሙሉ ወደነበረበት ለመመለስ የሚያደርጋቸውን ዕቅዶች ለማጠናቀቅ መስራቱን ቀጥሏል። በዚህ ምክንያትም፣ የሜትሮ ባቡር አገልግሎት አሁን ባለው የተቀነሰ የአገልግሎት ደረጃ ቢያንስእስከ ጥቅምት 31፣ 2021 ድረስ ይቆያል።

በዚህ ጊዜ፤ ባቡሮች በየ15-20 ደቂቃው በቀይ መስመር ላይ እና በየ30-40 ደቂቃው በሁሉም መስመሮች ላይ መሰረታዊ አገልግሎት ይሰጣሉ። የብራማ መስመር አገልግሎት በምስራቅ ዊህሌ-ሬስተን ( Wiehle-Reston East) እና በፌደራል ሴንተር (Federal Center) SW መካከል ብቻ መስራቱን ይቀጥላል። ደንበኞች ለእነርሱ የሚስማማ ሁኔታን የሚሰጥ በመሰላቸው ጊዜ የሜትሮባስ አገልግሎትን እንደ አማራጭ እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

የሜትሮ ዋና ሥራ አስኪያጅ Paul J. Wiedefeld "በክልሉ ውስጥ ሜትሮ በጣም ለሚጠቀሙ ሰዎች አስቸጋሪ ሳምንት እንደነበር የምንረዳ ሲሆን፣ ደንበኞቻችን እያጋጠሟቸው ያሉትን ፈተናዎችም እንገነዘባለን፣" ብለዋል። "በ 7000-ሲሪየስ የባቡር ተሽከርካሪዎች ላይ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ለመመርመር በተቻለ ፍጥነት እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እየሰራን ሲሆን፣ ይህንን በትክክል ማሳካት መቻላችንም በጣም አስፈላጊ ነው።"

የ7000-ሲሪየስ ስሪት የሆኑት 748ቱም ተሽከርካሪዎች በሙሉ ከስምሪት ውጭ በመሆናቸው የተፈጠረውን የባቡር እጥረት ለመቅረፍ ሜትሮ ተጨማሪ ባቡሮችን ወደ አገልግሎት ለማቅረብ የተቻለውን ሁሉ ጥረት እያደረገ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል 2000-ሲሪየስ የባቡር ተሽከርካሪዎች ከመጋዘን እና 6000-ሲሪየስ የባቡር ተሽከርካሪዎች ደግሞ በጥገና ላይ ይገኛሉ።

የፍተሻ ሂደቱን ለማጠናቀቅ ሜትሮ ከዋሽንግተን ሜትሮሬይል ደህንነት ኮሚሽን እና ከ7000-ሲሪየስ የባቡር ተሽከርካሪ አምራች ከሆነው ካዋሳኪ (Kawasaki) ጋር በጋራ እየሰራ ነው። እስካሁን ድረስ በ 7000-ሲሪየስ ተሽከርካሪዎች ውስጥ ከ 100 በስተቀር ሁሉም መኪናዎች ተፈትሸዋል።

ባለ 7000-ሲሪየስ ተሽከርካሪዎችን ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ወደ አገልግሎት ለመመለስ ሜትሮ አዳዲስ እቅዶችን እና የፍተሻ ሂደቶችን በማዘጋጀት ላይ ሲሆን እነዚህም ጎማው/መሪው ትክክለኛ አቀማመጡን መጠበቁን በምን ያህል ጊዜ መፈተሽ እንዳለበት ለማወቅ አዲስ መረጃ በመጠቀም የፍተሻውን ድግግሞሽ መገምገምን ይጨምራል። ባለ 7000-ሲሪየስ የባቡር ተሽከርካሪዎች በኢንዱስትሪ ደረጃ መሰረት በየ90 ቀኑ ፍተሻ ሲደረግባቸው ነበር።

የባቡር ተሽከርካሪዎች ወደ አገልግሎት ለመመለስ ዝግጁ ከሆኑ በኋላ፤ የባቡር ተሽከርካሪዎች እና መሳሪያዎች በሲስተሙ ውስጥ በትክክል መመደባቸውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ የሎጅስቲክስ ስራ ያስፈልጋል። ይህ የባቡር ተሽከርካሪዎችን ወደ ሜትሮ ባቡር ማቆሚያዎች እንደገና ማሰራጨት እና አዲስ የፍተሻ መርሃ ግብሮችን እንደ መደበኛ የመንገደኞች አገልግሎት ታሳቢ ማድረግን ይጠይቃል።

በአገልግሎት ቅነሳ ምክንያት፤ ደንበኞች ሙሉ የባቡር ተሽከርካሪዎች፣ አውቶቡሶች እና ጣቢያዎች ሊያጋጥማቸው ይችላል። ሜትሮ በባቡር ተሽከርካሪዎች፣ አውቶቡሶች፣ ጣቢያዎች እና ሌሎች የሜትሮ መገልገያዎች ላይ የአየር ማጣሪያዎችን አሻሽሏል። የሜትሮ ባቡር ተሽከርካሪዎች አየሩን በየሶስት ደቂቃው ያህል ቀይረው ይጠቀማሉ። ለማስታወስ ያህል፤ በመላው ስርዓቱ ላይ <u>የፊት ጭንብል ማድረግ አስገዳጅነቱ የሚቀጥል ነው።</u>

ደንበኞች የጊዜ ሰሌዳ መረጃ ለማግኘት የሜትሮ የጉዞ እቅድ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ። <u>የሜትሮ ጉዞ ዕቅድ አውጭ</u> አሁን ያለውን የጊዜ ሰሌዳ መረጃ የያዘ ሲሆን፣ የሜትሮ <u>የቀጥታ ባቡር ካርታ</u> ባቡሮች በመስመሩ ላይ ያሉበትን ትክክለኛ አስመልክቶ ትክክለኛ መረጃን ይሰጣል፤ ይህም ደንበኞች ለጉዟቸው በተሻለ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ያስችላቸዋል።

ሜትሮ አገልግሎቱ ሙሉ ለሙሉ መቼ እንደሚጀምር እስካሁን ትክክለኛ መረጃ የለውም። ስለ አገልግሎት እና ወቅታዊ መረጃ በMetroAlerts አጭር የጽሑፍ መልእክት ወይም የኢሜይል መልእክቶች፣ በTwitter @MetrorailInfo እና በwmata.com አሁናዊ ሁኔታ እና ማንቂያዎች ገጽ በኩል ለደንበኞች ይገለጻሉ።

ከዚህም ሌላ፣ ተጨማሪ መረጃ በሜትሮ ባቡር አገልግሎት እና ከሀዲድ ስቶ መውጣት ምርመራ ወቅታዊ መረጃ ላይም ይገኛል።